የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፳፭
አዲስ አበባ መጋቢት ፳፱ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

28th Year No. 25
ADDIS ABABA 7th April, 2022

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፭፻፫/፳፻፲፬

የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩትን አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባራትን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ.......................................ገጽ ፲፬ሺ፩፻፴፯

## Content

Regulation No. 503 /2022

The Council of Ministers Regulation to Determine the Organization, Power and Duties of Animal Health Institute ............Page 14137

### ደንብ ቁጥር ፭፻፫/፳፻፲፬

**<u>የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩትን አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባራትን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፫/፳፻፲፬ አንቀጽ ፵፮ (፪) መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ ደንብ "የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩትን አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባራትን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፭፻፫/፳፻፲፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### REGULATION NO 503/2022

**<u>COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO DETERMINE THE ORGANIZATION, POWER AND DUTIES OF THE ANIMAL HEALTH INSTITUTE</u>**

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 46 (2) of the Definition of Power and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 1263/2021.

**1. <u>Short Title</u>**

This Regulation may be cited as "The Council of Ministers Regulation No. 503/2022 to Determine the Organization, Power and Duties of Animal Health Institute"



CamScanner

## ፪. ትርጓሜ

በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፦

፩/ "እንስሳት" ማለት አጥቢ እንስሳት፣ በውሃ አካላት ውስጥ የሚኖሩ እንስሳት፣ አእዋፋት፣ እና ንቦችን ያካትታል፤

፪/ "ነፍሳት" ማለት የእንስሳት ጤና ጠንቅ የሆነ በሽታ አምጪ ተህዋስያንን ተሸካሚና አስተላላፊ የሆኑ የቆላ ዝንብ፣ ትንኞችና ሌሎች የውጪ ጥገኞችን ያጠቃልላል፤

፫/ "ምርመራ" ማለት ከእንስሳት፣ ከእንስሳት ምርቶችና ተዋፅዖዎች፣ ነፍሳት፣ ከዕጽዋት፣ ወይም ሌሎች አስፈላጊውን ናሙና በመውሰድ ተቀባይነት ያለውን ሳይንሳዊ ዘዴ በመጠቀም የእንስሳት በሽታ አምጪ ተህዋሲያንን ወይም የተህዋሲያንን ጠቋሚ ንጥረ ነገር ለመለየት የሚከናወን ሥራ ነው፤

፬/ "ምርምር" ማለት ሳይንሳዊ ዘዴን በመጠቀም በእንስሳት ጤና ችግር ዙሪያ መፍትሔ ለማምጣት የሚካሄድ ጥናት ነው፤

፭/ "ተቀባይነት ያለው ምርመራ" ማለት በዓለም አቀፍ የላቦራቶሪዎች እውቅና ሰጪ ድርጅት በታወቀ አካል እውቅና የተሰጠዉ የላቦራቶሪ ምርመራ ነው፤

፮/ "በሽታ" ማለት ማንኛውም የእንስሳት ጤናን የሚያውክ የእንስሳት የጤና ችግር ነው፤

፯/ "የበሽታ ክስተት" ማለት በተወሰነ አካባቢ አንድ ወይም ከአንድ በላይ እንስሳት በበሽታ ሲጠቃ ነው፤

## 2. Definition

In this Regulation unless the context otherwise requires:

1/ "Animal" includes mammals, animal in water bodies, birds and bees;

2/ "Insects" include tsetse flies and other vectors that carry and transmit animal disease causing agents;

3/ "Diagnostics" means laboratory tests and investigative activities performed using standard procedures on samples from animals, animal products, from insect vectors, plants or others to identify the animal disease causative agent itself or indicators of the agent;

4/ "Research" means a scientific study systematically conducted to bring solution for animal health problem;

5/ "Accredited test" means a laborator test method that has got acceptanc by accreditation body recognized by International Laboratory Accreditation Cooperation;

6/ "Disease" means any harmful deviation from the normal state in animals;

7/ "Disease outbreak" means the occurrence of one or more animal cases in an epidemiological unit;

CamScanner

፰/ "ድንበር ዘለል የእንስሳት በሽታ" ማለት ድንበር ሳይገድበው በከፍተኛ ደረጃ የመሰራጨት አቅም ያለው ተዛማች የእንስሳት በሽታ ነው፤

፱/ "ተዛማች የእንስሳት በሽታ" ማለት በእንስሳት ላይ ህመም ወይም እልቂት የሚያስከትል፣ ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፍ፣ የእንስሳት በሽታ ነው፤

፲/ "ሪፈራል ምርመራ" ማለት የክልል የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎች እና ሌሎች በእንስሳት ጤና ምርመራ ሥራ ላይ እውቅና ያላቸው አካላት የበሽታን መንስዔ መለየት ሲያዳግታቸው አስፈላጊውን ናሙናና መረጃ በመላክ በኢንስቲትዩቱ የሚሰጥ የመጨረሻ ምርመራ ነው፤

፲፩/ "ባዮሎጂካል" ለላቦራቶሪ ወይም ለቆላ ዝንብ እርባታ አገልግሎት የሚውል የምርመራ ግብዓት፣ ክትባት፣ የዝንብ ዝርያና የእንስሳት ደምን ያጠቃልላል፤

፲፪/ "ቴክኖሎጂ" የእንስሳት በሽታን ለመመርመር፣ ለመቆጣጠርና ለማጥፋት ጥቅም ላይ የሚውል ሳይንሳዊ ዘዴ፣ መሣሪያ እና የአሠራር ሥርዓትን ያጠቃልላል፤

፲፫/ "ጨረራ" ማለት ጋማ፣ ብርሃን፣ ታህተቀይ እና ልእለ ሀምራዊ የጨረር ኃይልን ያካትታል፤

፲፬/ "ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር" ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የግብርና ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

8/ "Transboundary animal disease" means highly contagious epidemic animal disease that has the potential for very rapid spread irrespective of national borders;

9/ "Epidemic animal disease" means diseases that have a potential to cause illness or tremendous animal death or zoonosis;

10/ "Referral diagnostic" means a referral test service delivered by the Institute when the diagnostic capacity is beyond the Regional Veterinary Laboratories or other bodies that are recognized in delivering animal health diagnostic service;

11/ "Biological" includes laboratory inputs, vaccine, fly species and animal blood used for the purpose of laboratory or tsetse fly mass rearing;

12/ "Technology" includes scientific method, equipment and standards used for diagnostic, control and eradication of animal disease;

13/ "Radiation" includes gamma, visible, infrared and ultraviolet rays;

14/ "Ministry" or "Minister" means the Ministry or the Minister of Agriculture respectively;

CS CamScanner

፪/ በቆላ ዝንብና በገንዲ በሽታ በተጠቁ የሀገሪቱ አካባቢዎች የመከላከል፣ የመቆጣጠር እና ማጥፋት ሥራዎችን በተጠናከረ መልኩ በማካሄድ የእንስሳትን ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣

፫/ በእንስሳት ጤና ላይ የስልጠናና የማማከር ሥራዎችን በማከናወን በዘርፉ የተሰማሩ ባለድርሻ አካላትን አቅም እንዲጎለብት ማድረግ ነው፡፡

፭/ <u>ሥልጣንና ተግባራት</u>

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበረሰባዊና አካባቢያዊ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ የእንስሳት ጤና ችግሮች ላይ የሚካሄድ ምርምርን ያስተባብራል፣ የምርምርና ስርፀት ሥራዎችን ያካሂዳል፣ ይገመግማል፣ ያስተዋውቃል፣ የፖሊሲ ሃሳቦችን ያቀርባል፣

፪/ በምርምርና ምርመራ ግኝት መሠረት የእንስሳት በሽታ ቁጥጥር ስልት በመለየት ምክረ-ሃሳብ ያቀርባል፣

፫/ ከሌላ ሀገር በእንስሳት ጤና ምርምር የተገኘ ቴክኖሎጂን ያላምዳል፣

፬/ በባህላዊና ዘመናዊ የእንስሳት መድኃኒት ላይ ምርምር ያካሂዳል፣

፭/ በሀገር ውስጥ የእንስሳት ጤና የሪፈራል ምርመራ ላቦራቶሪ በመሆን የመጨረሻ ማረጋገጫ ይሰጣል፣

2/ To enhance livestock production and productivity by applying prevention, control and eradication measures in areas affected by tsetse fly and trypanosomosis;

3/ To develop the capacity of stakeholders involved in the sector through provision of training and consultancy services on animal health.

5. <u>**Power and Duties**</u>

The Institute shall have the following powers and duties:

1/ Coordinate researches on animal health problems causing negative impact on the economy, public health and environment; conduct research and development activities, evaluate and promote research outcomes and provide policy ideas;

2/ Identify animal disease control strategies based on research and diagnostic findings and provide recommendation;

3/ Adapt animal health research technologies from other countries;

4/ Conduct research on traditional and modern medicine;

5/ Deliver referral diagnostic services on animal health and provide confirmation and approval of final diagnostic test result in the country;

CS CamScanner

፮/ በሀገራችን ዉስጥ ለሚገኙና ድንበር ዘለል ለሆኑ የእንስሳት በሽታዎች እና ነፍሳት፣ አዳዲስና ተደጋግመው የሚከሰቱ የእንስሳት በሽታዎች የመከላከልና ቁጥጥር ሥራዎችን ለመደገፍ የስጋት ትንተና፣ አሰሳና ቅኝት፣ እና የበሽታ ስርጭትና የጉዳት መጠን ግምገማ ያካሂዳል፤

6/ To support animal disease prevention and control activities on endemic disease, transboundary animal diseases and vectors, emerging and re-emerging diseases, it shall conduct risk analysis, surveillance and monitoring, disease distribution and impact assessment;

፯/ የእንስሳት በሽታ ክስተት መንስዔን ይለያል፣ ግንዛቤ ያስጨብጣል፣ ያስጠነቅቃል፣ እንዲሁም መረጃዎችን ያሰራጫል፤

7/ Identify the cause of animal disease outbreak, create awareness, provide warning and disseminate information;

፰/ ከእንስሳት ወደ ሰው በሚተላለፉ የእንስሳት በሽታዎች ላይ የምርምርና ምርመራ፣ እንዲሁም የግንዛቤ ማስጨበጫ ተግባራትን ያከናውናል፤

8/ Conduct research and diagnostic services and create awareness on zoonotic diseases;

፱/ ለእንስሳት በሽታ ምርመራ የሚያገለ የላቦራቶሪ ግብዓት ያበለጽጋል፣ ቴክኖሎጂ ያመነጫል፣ ውጤታማነቱን ያረጋግጣል፣ ጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ በግብዓት ማበልጸግና ማምረት ሥራ ላይ የተሰማሩ ተቋማትን ያበረታታል፤

9/ Develop Veterinary laboratory diagnostic inputs, innovate technology, conduct validation, ensure their utilization, encourage others involved in input development and production;

፲/ እንስሳት ወደ ሌላ ሀገር በሚላከበት ጊዜ ወይም ወደ ሀገራችን ሲገባ በሚቀርብ ጥያቄ መሠረት የጤንነት ማረጋገጫ ምርመራ ያካሂዳል፤ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው የምርመራ ውጤት ይሰጣል፤

10/ Conduct laboratory test and issue internationally acceptable test results as per a request for certification of export or import of animals;

፲፩/ የክልል እንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎችን አቅም ለማጎልበት በትብብር ይሰራል፤

11/ Work, in collaboration, to build the capacity of the Regional Veterinary Laboratories;

